National Meteorological Agency
ETHIOPIA

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከሰፕቴምበር 1-30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከኦክቶበር 1-31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2021
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ....... 3
ጠባይ ግምገማ ....... 3
ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 4
ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 5
ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 6
እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ....... 7
ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 7
ካርታ 9 ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 7
እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ . 8
ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 8
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው ....... 9
የአየር ጠባይ አዝማሚያ ....... 9
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 9
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 10


## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የሴፕቴምበር ወር ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የተሻለ ገፅጻታ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በተለይም በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተስፋፉ የዝናብ ስርጭት ነበራቸዉ፡፡ ይሁን እንጂ  ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በመዳከማቸዉ በሶስተኛዉ አስር ቀናት ዝናቡ በመጠንም ሆን በስርጭት ረገድ ከአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የሴፕቴምበር ወር በተለያዩ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአማራ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና በጋምቤላ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በሻምቡ 39.2፣ በበደሌ 43.8፣ በአልጌ 54.0፣ በነቀምቴ 37.4፣ በጉንደመስቀል 71.2፣ በጊዳ አያና 45.4፣ በቤጊ 41.4፣ በጅማ 38.8፣ በአማን 68.5፣ በኮንሶ 34.4፣ በባህር ዳር 36.3፣ በማሻ 30.2፣ በአዲስ አበባ 34.4 እና በአሶሳ 36.7ና 46.5፣ በማንኩሽ 46.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፈዉ የሴፕቴምበር ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በአርሲና ባሌ፣ በሁሉም የሸዋና ወለጋ ዞኖች፣ በኢሉባቦርና ጅማ ዞኖች፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፣ በሲዳማ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ100-463 ሚ.ሜ. የሚደርሰ ዝናብ ከ10-28 ቀናት ያህል ዝናብ የዘነበ ሲሆን፤ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከ5-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ከስድስት ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

ባለዉ የሴፕቴምበር ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከመተከል ዞን በስተቀር በተቀሩት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፣ በሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከጥቂት የቦረና ዞን በስተቀር በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ላይ፣ በደቡብ ብሄር ቤሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከሞላ ጎደል በሁሉም የአማራ ክልል ዞኖች ላይ፣ ከአፋር ክልል ዞን 04፣ 05፣ 01ና 03፣ በሲዳማ ክልል እና ከዋርዴር ዞን በስተቀር በሁሉም የሱማሌ ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 8)፡፡


ካርታ 6   ኢ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች መደበኛ ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከሰፐቴበር 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የነበሩ በመሆኑ በተለይም በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ የተተነተኑ ወርኃዊ የአፈር ውስጥ እርጥበት ጠቋሚ መለኪያ (Moisture Index) እንደሚያመለክተው በተለይም በምዕራብ አጋማሽ፣ በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅና በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎችን የሸፈነ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውኃ ከማቅረብ አንጻር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ እንዲሁም ቀስ በቀስም ወደ ደቡብ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋዉ የእርጥበት ሁኔታ በደጋማው አካባቢ የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና ነበረው፡፡ በአንፃሩም በሶስተኛዉ አስር ቀናት እርጥበታማው ሁኔታ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ ከአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀንሶ የነበረ በመሆኑ አስቀድመው ለተዘሩና እድገታቸውን ጨርሰው ለነበሩ ሰብሎችም ሆነ በአንዳንድ ቆላማ አካባቢዎች ላይ እየተከናወነ ለነበረው የሰብል ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ አዎንታዊ ጎን ነበረው፡፡ በሌላም በኩል ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአማራ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና በጋምቤላ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት በሚታወቁ ሰፍራዎች ላይ ተከታታይነት የነበረው እርጥበታማ ሁኔታ በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ያስከተለ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘዉ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 9)፡፡


ካርታ 9 ከሰፐቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-30 ሴፕተምበር 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በምዕራብ፣ በመካከለኛውና በደቡባዊ የአገሪቱ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል። በዚህም መሰረት ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ባሮአኮቦ፣ አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ ተከዜ፣ ዋቢሸበሌ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ እና የላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ሲሆኑ፤ የመካከለኛው ዋቢሸበሌና የመካከለኛው ገናሌዳዋ፣ ምስራቃዊ ተከዜና የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ደግሞ መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ናቸው። በሴፕቴምበር ወር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ ዝናቡ በመጠኑ ከፍተኛ በመሆኑ በእንዳንድ ተፋሰሶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ቢኖረውም፤ ለዉሃ ሀብት ዘለቄታ አገልግሎት ጠቃሚ ገፅታ ነበረው።

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከሰፕቴበር 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ድንበር ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ስለሚሄዱ የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው የበጋ ወቅት እንደሚስተዋለው የሰሜን አጋማሽ የኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ከመታየቱ አንጻር የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመር ያሳያል፡፡

በሚቀጥለው ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህም ሌላ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጨምር ይችላል እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ በመጪው ወር <u>ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ አርሲ፣ ባሌና የጉጂ ዞኖች፣ ምዕራብ ሐረርጌ፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ እንዲሁም የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የወላይታ እና የደቡብ ኦሞ፣ የጉራጌ፣ የጌዲዮ እንዲሁም የሲዳማ ክልል በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ እና በጥቂት ሥፍራዎች ደግሞ ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ጠንካራ ደመናዎች በሰሜንና በደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ እንዲሁም አፋር ዞን 3 እና 5፤ የቦረናና ምስራቅ ሐረርጌ፤ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ አዲስአባባ፤ ጋምቤላ ክልል፤ የሰገን ህዝቦችና ደቡብ ኦሞ እንዲሁም ከሶማሌ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች አነስተኛ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦክቶበር ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው ከላይ የተገለፀው የትንበያ መረጃ

ያመለክታል። ይህም ሁኔታ ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩትና ሰብል አምራች በሆኑት በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ቀደም ብሎ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በስፋት በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደሚኖረው ይጠበቃል። በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት የሚኖረው በመሆኑ ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ደረጃቸውን ላልጨረሱ ለመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በአካባቢው ለሚገኙ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች፣ ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ ሣር ልምላሜ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በተጨማሪም በአብዛኛው የሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ሊታይ እንደሚችልና ይህም ሁኔታ በተለይም በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ የደጋውና የወይና ደጋ የአገሪቱ ክፍሎች ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን፤ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል በመጠበቁ በመደበኛ ሁኔታ በበጋ ወቅት ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በመከሰት ሣቢያ የሚፈጠር ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሰሜን የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች የመከሰት እድል ሊኖር ስለሚችል ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል።

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ኦክቶበር የበጋ የመጀመሪያ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚህም መሰረት በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ እንዲሁም ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች እርጥበታማና በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም በአብዛኛው አዋሽ፣ ምስራቃዊ አባይ፣ የታችኛው ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ፣ የታችኛው ባሮአኮቦ እና የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች አነስተኛ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡